# የቅድመ-መዋእለ ህፃናት/ሄድ ስታርት ፕሮግራሞች የትምህርት ዓመት 2026–2027 ሠነዶች ዝርዝር

Prekindergarten/Head Start Programs School Year 2026–2027 List of Documents

Department of Early Childhood, Federal and Special Programs
Rocking Horse Road Center, 4910 Macon Road, Room 143, Rockville, Maryland 20852

ParentVue ወይም www.montgomeryschoolsmd.org ላይ ማመልከቻዎችን ማቅረብ ይቻላል። ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር:- 240-740-4530 ይደውሉ። ቅድመ ሙአለህፃናት/ሄድስታርት ለሚመዘገቡ ልጆች፣ የአካል ስንክልና ያላቸውን ህጻናት ጨምሮ ከሰኞ እስከ ዓርብ 9:00 a.m. እስከ 4:00 p.m. በሚከተለው አድራሻ የማመልከቻ ቅጽ ያለቀጠሮ በአካል ማቅረብ ይቻላል። አድራሻ:- Rocking Horse Road Center, 4910 Macon Road, Rockville, Maryland, 20852

**ማመልከቻውን ለመሙላት፣ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ሠነዶች ማቅረብ አለብዎት።**

የሚከተለውን ዝርዝር በመመሪያነት ይጠቀሙ:-

❑ 1. የተማሪ የእድሜ ማረጋገጫ እና መታወቂያ— ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ሠነዶች/ዶኩመንቶች አንዱን ያቅርቡ።
- የልደት ሠርተፊኬት
- ፓስፖርት
- የሃኪም ሠርተፊኬት
- የጥምቀት ወይም የቤተክርስቲያን ሠርተፊኬት
- የሆስፒታል ሠርተፊኬት
- የሠነድ ማረጋገጫ/ኖቶራይዝ የተደረገ የወላጅ ቃለመኃላ/affidavit
- የልደት ምዝገባ ሠርተፊኬት፣ ወይም
- ሌሎች ህጋዊ የሆኑ ወይም የሠነድ ማረጋገጫ/ኖቶራይዝ የተደረጉ የልጆች መታወቂያ እና የልደት ቀን ማረጋገጫ ሠርተፊኬት።

❑ 2. ተማሪው(ዋ)ን ወደ ትምህርት ቤት የሚያስገባው/የምታስገባው ሰው መታወቂያ እና ከተማሪው(ዋ) ጋር ያለ ግንኙነት—
ፎተግራፍ ያለበት የማንነት መታወቂያ ለምሳሌ:—ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት አንዱን ማቅረብ ይቻላል።
- የመንጃ ፈቃድ
- ፓስፖርት
- ከሞተር ተሽከርካሪዎች አስተዳደር (MVA) የተሰጠ መታወቂያ ካርድ።
- ሌላ ህጋዊ መታወቂያ

ከተማሪ ጋር ያለ ግንኙነትን በሚመለከት የሚካተቱ ምሣሌዎች—ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ሠነዶች አንዱን ያቅርቡ።
- የልጅ የልደት ሠርተፊኬት
- የፍርድ ቤት ትዕዛዝ/ውሳኔ
- ለመለያየት የተደረገ ስምምነት ወይም የፍቺ ሠነድ፣ ወይም
- ሌላ ህጋዊ መታወቂያ

❑ 3. የቤተሰብ የገቢ ማረጋገጫ (ጎልማሳ የቤተሰብ አባላት በሙሉ)— ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ሠነዶች እርስዎን የሚመለከቱ ሠነዶችን በሙሉ ያቅርቡ።
ለምሳሌ:- ከዚህ በታች ያሉትን ያካትታል።-
- 2025 ታክስ የተሠራበት ቅጽ/Tax return for 2025—1040, W2s, Schedule C/1099
- ሦስት ወቅታዊ የደሞዝ (ቼኮች) ክፍያ ሠነዶች/pay stubs
- የሥራ ቅጥር ደብዳቤ
- ስለ ልጅ ማሳደጊያ ድጋፍ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተሰጠበት ደብዳቤ ወይም ውሳኔ
- የዶላር መጠን የሚያሳይ የፋይናንስ እርዳታ ደብዳቤ
- ጊዜያዊ የገንዘብ ድጎማ (TCA)
- የኪራይ ገቢ ደብዳቤዎች
- የሥራ አጥነት፣ የአካል ስንክልና ገቢ፣ ወዘተ

❑ 4. ወቅታዊ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪነት ማስረጃ
- የግል መኖሪያ ቤት ባለቤት ከሆኑ—ተቀባይነት የሚኖረው ወቅታዊ የንብረት ታክስ ሠነድ ነው
- ቤትዎ የተከራዩት ከሆነ—ተቀባይነት የሚኖረው ወቅታዊ የኪራይ ውል/ሊዝ ነው* (የሚመለከትዎ ከሆነ፣ HOC የኪራይ ወይም ዩቲሊቲ ድጋፍ የሚሰጥዎት ከሆነ ሠነዱን አባሪ አድርገው ያቅርቡ)።
  *ኦርጅናል የሊዝ ስምምነት ያበቃለት ከሆነ፣ የሊዙን ቅጂ እና ወቅታዊ ዩቲሊቲ ቢል ያቅርቡ
- MCPS ትምህርት ቤት አካባቢ በህጋዊነት ኗሪ ከሆነ/ች የቤት ባለቤት ጋር ወይም ከተከራይ ጋር በደባልነት የሚኖሩ ከሆነ—
- የሠነድ ማረጋገጫ ማህተም/ኖቶራይዝ የተደረገ MCPS ቅጽ 335-74፣የመኖሪያ ቤት ደባልነት መግለጫ/Shared Housing Disclosureበአግባብ ተሞልቶ መቅረብ አለበት፣ የቤት ባለቤትነት ወቅታዊ የንብረት ታክስ ሠነድ/ቢል ቅጂ፣ ወይም የመኖሪያ ቤት ኪራይ-ሊዝ ቅጂ (ኦርጅናል የኪራይ ውል/ሊዝ ጊዜው ያለፈበት ከሆነ፣ የሊዝ ውል ቅጂ እና ዩቲሊቲ ክፍያ ሠነድ-ቢል)፣ ተፈርሞበት ኖቶራይዝ የተደረገ የ MCPS Form 335-74፣ እና ወላጅ/ሞግዚት ወይም ብቁነት ያለው/ያላት ተማሪ በተገለጸው አድራሻ ነዋሪ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ሦስት ዶኩሜንቶችን ማቅረብ። MCPS ቅጽ 335-74 ተሞልቶ እና ተፈርሞበት ህጋዊ ሰነድ መሆኑን ሲፈረም በሠነድ ማረጋገጫ የተረጋገጠ/notarized ከሆነ አድራሻ ለማረጋገጥ ከሦስቱ አስፈላጊ ማረጋገጫዎች አንዱ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል።

❑ 5 ለእርስዎ አስፈላጊ ከሆነ ብቻ የሚከተሉትን ማስረጃዎች/ሠነዶች ያቅርቡ
- የልጁ-የልጅቱ የህክምና ኢንሹራንስ ካርድ
- WIC Folder/ፋይል
- የተመጣጣኝ ምግብ እርዳታ ፕሮግራም (SNAP) ደብዳቤ (የቀድሞው ፉድስታምፕስ)
- የልጅ እንክብካቤ ስኮላርሺፕ ቫውቸር
- የልጅ ተንከባካቢ ስም እና አድራሻ
- የሕፃን ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP)፣ የአሳዳጊነት/የማደጎ/የሞግዚትነት ማረጋገጫ

Child's Individualized Education Program (IEP)፣ proof of guardianship/foster care/custody